# ስለ ልሣነ ግፉዓን (Voice of the Victims) ድርጅት መቋቋም

## የተሰጠ መግለጫ።

በዉጭ አገር የምንገኝ የወልቃይት ፀገዴ ተወላጅ ኢትዮጵያዉያን፣ የጠባብ ብሄርተኛዋ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አዉጭ ድርጅት በኢትዮጵያዉያንና በኢትዮጵያ አገራችን እያደረሰች ያለዉን ጭካኔ የበዛበት ግፍና በደል፣ ከሌላዉ ኢትዮጵያዊ ወገናችን ጎን በመሰለፍ ገና ክጅምሩ አንስተን እስከ አሁኗ ሰዓት ድረስ ይህን እኩይ ድርጊት እየተቃወምንና እያወገዝን ብሎም እየታገልን እንገኛለን።

የትግራይ ሕዝብ ነፃ አዉጭ ግንባር "ታላቋን ትግራይ" ለመገንባት ባላት ምኞት ከጎንደር ክፍለ ሃገር ታሪካዊና ለም አካል የሆኑት የወልቃይት ፀገዴና የጠለምት ግዛቶች በማን አለብኝነት በመንጠቅ ወደ ትግራይ ክልል ቀላቀለች። ወያኔ በትረ መንግሥቱን ከጨበጠች በኃላም፣ መንግስታዊ ኃይሏን በመጠቀም በሦስት ዓላማዎች ያንጣጠረ ማለትም፣

1. በኃይል ለወሰደችው መሬት ተጠያቂ ላለመሆን፣
2. መንግሥታዊ ሥልጣኑን ከመጨበጧ በፊት በጀግንነትና በቆራጥነት የተፋለማትን ሕዝብ ቂም ለመበቀል፤
3. የሰሜን ምእራብ ኢትዮጵያ ደንበር ጠባቂ አልባ ለማስቀረት ሲባል፤

በዚህ ጀግና የወልቃይትና ፀገዴ ተወላጅ ኢትዮጵያዊ ወገን ላይ ከፈተኛና ማቆሚያ የለለው ጥቃት እየፈፀመች ትገኛለች።

ወያኔ " አንድን ወገን አጥፈቶ በሌላ የመተካት" (Genocide) ዘዴ በመጠቀም ስልት የተሞላበት ከፍተኛ የጥቃት ዘመቻ በወልቃትይ ፀገዴ ሕዝብ ላይ አካሄዳለች፤ በብዙ ሺ የሚገመቱ ወገኖች አስራለች፣ ገድላለች፣ ከቀያቸው አፈናቅላለች፤ ከ600,000ሺህ በላይ የትግራይ ተወላጆች ብቻ በወልቃይት ፀገዴ መሬት ላይ አስፍራለች አሁንም ለማስፈር ቦታዎችን እያመቻቼች ትገኛለች፤ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ እናቶችና እህቶችም በወያኔና ደጋፊዎቿ እየተደፈሩ ያለፍላጎት እንዲወልዱ ተደርጓል፤ ይህንን ሕገወጥ አስገድዶ የመድፈር ተግባርም ያለምንም ሃፍረት አጠናክረው ቀጥለውበታል። ከሞት ተርፎ መሔጃ አጥቶ በተወለደበት አካባቢ የቀረው ወገንም፤ እንደ ሁለተኛ ዜጋ አድርጎ በመቁጥር ነፃነት ሳይኖረው፣በድኽነትና በሰቃይ ውስጥ እንዲኖር እየተደረገ ነው።

እኛም በዚህ አካባቢ የተወለድን ኢትዮጵያዉያን ወያኔን በተለያየ ዘርፉ መታገል አስፈላጊ መሆኑን በማመን፤ ነውጠኛዋ ወያኔ በኢትዮጵያ በተለይ በወልቃይት ፀገዴ ሕዝብ ላይ የፈፀመችዉና እየፈፀመች ያለችዉን ከፍተኛ ወንጀል ማጋለጥ፣ ወንጀል የፈፀሙትን እብሪተኞች ወደ ፍርድ ለማቅረብ ተጨባጭ ማስረጃዎችን ማሰባሰብ፣ በዓለም ዙርያ የተበተኑትን የአካባቢው ተወላጆች በያሉበት ተደራጅተው የሚፈለግባቸውን ሁለንትናዊ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ እየተካሄደ ላለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አስተዋፅዖ ይኖረዋል በሚል እምነት፣ ልሳነ ግፉዓን (Voice of Victims) በመባል የሚታውቅ ድርጅት አቋቁመናል።

*ልሳነ ግፉዓን በአሜሪካ ዉስጥ በኦሃዮ ክፍለ ግዛት (State Of Ohio) ህጋዊ ፈቃድ አግኝቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።*

*የድርጅቱ ራዕይ፥*

*በአጠቃላይ በኢትዮጵያ በተለይም በወልቃይት ፀገዴ ዘላቂ የሆነ ፍትሕ፣ ሰላምና ነፃነት ሰፍኖ ማዬት።*

*የድርጅቱ ተግባራት፥*

*1ኛ/የትግራይ ሕዝብ ነፃ አዉጭ ግንባር (ወያኔ) እና መሪዎቿ በወልቃይት ፀገዴ ሕዝብ ላይ የፈፀሙትን "አንድን ሕዝብ አጥፍቶ በሌላ የመተካት ሴራ (Genocide) ማጋለጥና ተጠያቂዋ ወያኔና መሪዎቿም ወደ ፍርድ የሚቀርቡበት መንገድ ማመቻቸት፤ እንዲሁም የዚህ አይነት አሰቃቂ ድርጊት በሃገራችን በኢትዮጵያ እንዳይደገም ያለሰለሰ ጥረት ማድረግ፤*

*2ኛ/በግፍ የታሰሩ ወገኖች እንዲፈቱ መጣር፣*

*3ኛ/ በወያኔ አስከፊና አሰቃቂ ድርጊት ለተጎዱ ቤተሰቦች በሁለንተናዊ መንገድ መርዳት፤*

*4ኛ/የተዘረፈ የሕዝብ ንብረት ለባለ ንብረቱ፣የተቀማ መሬት ለባለ መሬቱ እንዲመለስ መታገል፤*

*5ኛ/ ወልቃይት ፀገዴ ወደ ነበረበት ወደ ጎንደር ክፍለ ሀገር እንዲቀላቀል ክፍተኛ ጥረት ማድረግ፤*

*6ኛ/ ለሃገሪቱም ሆነ ለአካባቢዋ ዘላቂ ፍትህ፣ ሰላም፣ ነፃነትና አንድነት ለማምጣት ለሚታገሉ ሃገራዊ ድርጅቶች ድጋፍ መስጠት ወዘተ…ሲሆን፤ ይህን የተቀደሰ ዓላማ ከግቡ ለማድረስ የጉዳዩ ባለቤት ከሆነዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ ተሳትፎና ድጋፍ ይጠይቃል። ድጋፋችሁና ትብብራችሁ ለመስጠትና ለመግለፅ የምትፈልጉ ወገኖች በቅርቡ (Web-Site) እንደሚኖረን እየገለፅን ለግዜዉ ግን ከዚህ በታች ባለው የኢሜል አድራሻ ልታገኙን ትችላላችሁ።*

*voiceofthevictims79@yahoo.com*

*ሰላም፣ፍትህ፣ነፃነትና አንድነት ለኢትዮጵያ !!!*
*ውድቀትና ሞት፣ ለነውጠኛዋ ወያኔ*

*ልሳነ ግፉዓን (Voice of Victims organization)።*